# የኢትዮጵያ አምላክ የት ሄዶ!

*ከአባዳማ ነጋ*

የኢትዮጵያ አምላክ የት ሄዶ ! መለኮታዊ ባውዛውን አብርቶ ፀረ- አገርና ፀረ- ሕዝብ ጠላቶችን አሳይቶናል።

ኦነግ በግፍ ሕዝብ ወደ ገደል እየወረወረ የፈጀና ጄኖሳይድ የፈፀመ በመሆኑ በአለም አቀፍ ደረጃና በወደፊቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ መንግሥት ታድኖ ለፍርድና ለቅጣት የሚቀርብ ወንጀለኛ ነው።

አብነግ ደግሞ በሐረርጌ በተለይም በጅጅጋና በኦጋዴን የኢትዮጵያ ሴቶችን ጡት በጭካኔ የቆረጠና ሰላማዊ ሕዝቡን በግፍ የፈጀ የሽብር ግንባር በመሆኑ በኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠየቅ ነው።

ግንቦት(7) ከነዚህ አረመኔዎች ጋር ተሻርኮ አብሮ በመስራት በኢትዮጵያ ላይ ወንጀል እየፈፀመ ነው። ይህ ድርጅት ወያኔና ሻቢያ አፍቃሪ በመሆኑ ኢትዮጵያና አንድነቷ እንደ ሬት ይመሩታል። ስለሆነም ተልዕኮው ሴፍ ኰንዳክት ለወያኔ ፈቅዶ ኦነግንና አብነግን አስገንጥሎ ለራሱ ክልል ፈጥሮ ሌላውን ማመሰቃቀልና መፍጀት ሊሆን እንደሚችል ድንፋታውና እንቅስቃሴው በጭላጭል እያሳዩን ነው። ግንቦት 7 የኢሳያስን የመቶ አመት የቤት ሥራ በኢትዮጵያ ላይ ለማሳካት ተወካዮችን አስመራ አስቀምጦ እየተመሳጠረ ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብና የአገር ወዳድ ኃይላት ቀዳሚና ያለመ ትኩረት ድርድር ሳይሆን ወያኔን ርዕዮቱን፣ ሥርዓቱን፣ መዋቅሩንና ድርጊቱን ሁሉ ጠራርጎ ሕልውና ማሳጣትና ያገርን ትንሳኤና ኢትዮጵያዊነትን ማረጋገጥ ነው።

አንዳንድ በሳይበር ላይ በግልጽም ሆነ በስውር የሚልመሰመሱ እንዲያው በከንቱ ይጥራሉ እንጅ ያገር ጠላቶች መደምሰሳቸው የማይቀር ነው።

ወያኔ በቀትር ወንዝ ወርዶ ሰይጣን ቢጐተት እንኳ ወይንም አባ ጳውሎስ መተት ቢያደርግ ውድቀቱ፣ መከስከሱና መመንገሉ በቅርቡ የማይቀር ክስተት ነው።

ስለዚህ ለአገር ለአንድነት የቆማችሁ ግለሰቦች፣ ስብስቦችና ኃይሎች ሁሉ ከውሽልሽል ሳይበር ፕሮፓጋንዳ፣ ከፍሬርማቶሪ ከጋዜጠኞች ወሸከታ፣ ካልጠለለ የምሁር ከንቱ ውዳሴ፣ ከሕብረት መካን ፖለቲካ በአጠቃላይ ከማይረባ ጭጫታዎችና ተጽኖዎች ራሳችሁን በአስቸኳይ አላቃችሁ በድህረ - ወያኔ ለሚጠበቅባችሁ ያገርና የወገን ግዳጆችና አገር ምሥረታ ዝግጁ ሆናችሁ እንድትገኙ ይጠበቅባችኋል።